# ዕቅዱ

“ኢንቪዥን ካምብሪጅ” ከመቼውም ጊዜ የላቀ ለመኖሪያነት ተስማሚ፣ ዘላቂ፣ እና ለሁሉም እኩል የሆነ ከተማ ለመገንባት  የሚያስችል አጠቃላይ ዕቅድ ለማውጣት የሚንቀሳቀስ የሦስት ዓመት ይፋዊ ሂደት ነው።

“ኢንቪዥን ካምብሪጅ” ከማህበረሰቡ በተገኘ ግብዓት፣ ለከተማው የወደፊት ራዕይ ስድስት ዋና ዋና የጋራ እሴቶችን አዘጋጅቷል።

ውይይቱን በሚከተለው ሊንክ ይቀላቀሉ
**envision.cambridgema.gov**

@CDDat344 facebook.com/CDDat344

## ተሳትፎዎቹ በቁጥሮች ሲገለጹ!

**2,510**
በተንቀሳቃሽ ስልክ የተሳትፎ ጣቢያ ተደራሽ የሆኑ ሰዎች

**1,706**
በኦን ላይን እና በአካል የተደረጉ ጥናቶች (ሰርቬይ) ምላሾች

**2,372**
በማኅበራዊ ድህረ ገጾች የተደረጉ ግንኙነቶች

**211**
የጥናት (ወርክሾፕ) ተሳታፊዎች

**119**
ዝቅተኛ ተደራሽነት ባላቸው ህዝቦች ላይ ያነጣጠረ ተሳትፎ

**16**
ጥናቶችን፣ ፓናሎችን፣ እና የሥራ የቡድን ውይይቶችን ጨምሮ የህዝብ ስብሰባዎች

የተሳትፎ ማጠቃለያ፣ ከጁላይ 2016 ጀምሮ።

ሙሉ ዘገባውን ለማግኘት፣ በሚከተለው ሊንክ፣ “documents” የኒለውን ይጫኑ፥
envision.cambridgema.gov/documents/#summaries

ENVISION CAMBRIDGE

# ENVISION CAMBRIDGE




envision.cambridgema.gov

## ራዕያችን

ካምብሪጅ ተራማጅ አስተሳሰብ ያለው፣ ጋባዥ፣ እና ብዝሃነት ያለው ከተማ ነው። ህብረተሰቡ ከፍተኛ ጥራት ያለው ሕይወት የሚኖር ሲሆን፥ ቀጣይነት ያለው፣ ሁሉን አቀፍ የሆነ፣ እና እርስ በርሱ የተሳሰረ ማህበረሰብ እንዲኖረው ተግቶ ይሰራል።

## ዋና እሴቶቻችን

### ምቹነት

ማራኪ ሁኔታ እና ተፈጥሯዊ መንፈስ ለተላበሰ ግንባታ ትልቅ ዋጋ የምንሰጥ ሲሆን፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው እና ለተገልጋዩ የእለት ከእለት መዳረሻ እና የመዝናኛ ምንጭ የሆኑ ዘላቂነት ያላቸው መጓጓዣዎችን እንደግፋለን።

### ዘላቂነት እና ህዳሴ

በአካባቢ ላይ የምንፈጥረውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ እና ጠንካራ ከተማ እና ጠንካራ ማህበረሰብ ለመገንባት ሃላፊነትን እንወስዳለን።

### ብዝሃነት እና ፍትሐዊነት

እንግዳ ተቀባይ፣ ብዝሃነታችንን የምናከብር እና በተመጣጣኝ ዋጋ የመኖሪያ ቤት ምርጫዎች እንዲሁም የስኬታማነት እድሎች መኖር መቻላቸውን ለማረጋገጥ የምንተጋ ማህበረሰብ ነን።

### የማህበረሰብ ጤና እና ደህንነት

እርስ በእርሱ በሚደጋገፍ፣ ደህንነቱ በተጠበቀ እና ከማህበረሰቡ ጋር እንዲገናኙ እና በሕዝባዊ ሕይወት ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስችሉ የተለያዩ እድሎች ያሉትን ጤናማ እና ንቁ የአኗኗር ዘይቤን እናስተዋውቃለን።

### የኢኮኖሚ አማራጮች

ጥራት ያላቸው ስራዎች፣ የሰው ሃይል ልማትና ሥልጠና፣ እና ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን አገልግሎቶች  መደገፍ የሚያስችል የመኖሪያ ደመወዝ እንዲኖር በማድረግ፣ የተለያዩ እድሎችን እና የተረጋጋ ህይወትን እንሰጣለን።

### ትምህርት

ዘመናት ያስቆጠረ የትምህርት ባህል እና እውቀትን የሚሹን የሚያከብር፤ የባህል ሀብታም እና በፈጠራ የተካነ ማህበረሰብን ያቀፍን ነን።